6. ሐረር (ሀረሪ፣ ድሬዳዋ፣ ሶማሌ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሀረርጌ አካባቢዎች)
7. አሶሳ (ቤኒሻንጉል፣ ምዕራብ ወለጋ፣ጋምቤላና አዋሳኝ አካባቢዎች)

## አደረጃጃት

ማዕከላቱ የብዝኀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት ቅርንጫፎች ሆነው የተደራጁ ሲሆን ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለኢንስቲትዩቱ ነው። እነኚህ ማዕከላት የሚሰሩባቸው አካባቢዎች
ከሚገኙባቸው የክልል መስተዳድሮችና ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበትና በቅንጅት እየሰሩ ይገኛሉ።

## የማዕከላት ተግባርና ኃላፊነት

በተመረጡ አካባቢዎች የተቋቋሙት ማዕከላት ከኢንስቲትዩቱ ተግባርና ኃላፊነት በተዋረድ ተቆርሶ የተሰጣቸው ሲሆን ይህን ለማስፈጸም ኢንስቲትዩቱ ክትትልና ግምገማ ያደርጋል።

1. በአካባቢው የሚገኘውን የብዝኀ ሕይወት ሀብት በዘቦታ የሚጠበቅበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ መጠበቅ፤
2. በአካባቢው የጠፉ/ የተመናመኑ ዝርያዎች ተመልሰው የሚተኩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ መልሶ መተካትና ድጋፍ መስጠት፤
3. ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ብዝኀ ሕይወትን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ ማድረግ፤
4. ብዝኀ ሕይወት ጥበቃን በሚመለከት ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር በመተባበር መስራት፣
5. የብዝኀ ሕይወት ሀብቶች በመመዝገብና በተለይም ለጉዳት የተጋለጡትን በማጥናት የሚጠበቁበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
6. የሀገሪቱን ብዝኀ ሕይወት መጠንና ስርጭት የሚያበለጽጉ ወይም የሚያናጉ ክስተቶችን አስቀድሞ በመተንበይ ጤናማ ሂደቶችን ለማስቀጠልና የችግር ስጋቶችን ለመገደብ የሚያስችሉ ሀሳቦችን ለኢንስቲትዩቱና ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረብ፤
7. በጀነቲክ ሀብት አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ዙሪያ ተገልጋዮቹን ማጣከር፣ መረጃ ማሰባሰብ፣ ለአርክቦት ፈቃድ ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
8. በህብረተሰቡ ዘንድ ስለ ብዝኀ ሕይወት ሀብት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም ተገቢው ዕውቀት እንዲሰርጽ ከመገናኛ ብዙኀን ዘዴዎችና ከትምህርት ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የአህዝቦት ሥራ መስራት፤

## የፊቼ ጅን ባንክ ዋና ዋና ተግባራት

1. የዕፅዋት ዘር፣ የእንስሳትና የደቂቅ አካላት ናሙና ቅጂ ከአዲስ አበባው ዋና ጅን ባንክ ተቀብሎ ያነብራል
2. ደጋማ አካባቢ የአዝዕርትና ሆርቲካልቸር ዝርያዎች ዘር ያባዛል
3. የእንስሳት ወንዴ ዘር ለመሰብሰብ ወደ ጅን ባንኩ የሚመጡ እንስሳት ተለያይነትና የጥበቃ ዘዴዎች ላይ ምርምር ያካሂዳል፣ እንስሳቱን ይንከባከባል ፣ ዘራቸውን ይሰበስባል፣ ዘራቸውን በማዘጋጀት ያነብራል፣ ቅጂውን ወደ አዲስ አበባው ዋና ጂን ባንክ ይልካል
4. የችግኝ ጣቢያ ያቋቁማል፣የብዜት ችግር ያለባቸውን የዱር በቀል እፅዋት የማንበርና መልሶ የመተካት ዘዴ ላይ ምርምር ያደርጋል
5. ለአካባቢው ማህበረሰብ አገልግሎት የሚሰጥ ማህበራዊ ጅን ባንክ ያቋቁማል
6. የንብ ዝርያዎችን ይጠብቃል
7. የደጋ አካባቢ የዓሳ ዝርያዎችን ይጠብቃል
8. የደጋ አካባቢ ዕፅዋት በመሰብሰብ የዕፅዋት አፀድ እና ሄርባርየም ያቋቁማል
9. የእንስሳት ቅሪተ አካል ሙዚየም ያቋቁማል
10. በብዝኀ ሕይወት ላይ ምርምር ያካሄዳል፣
11. የአጭር ጊዜ ሥልጠና ይሠጣል

## የጅማና ሻሸመኔ ዕፅዋት አፀድ ኃላፊነት

1. በዕፅዋት ሥርጭትና ተለያይነት ላይ ምርምር ያደርጋል፣ ዕፅዋት በመሰብሰብ የዕፅዋት አፀድና ሄርባርየም ያቋቁማል ፣ የተመናመኑ ዕፅዋትን ያነብራል፣ ለትምህርትና ለአእምርእርካታ የጉብኝት አገልግሎት ይሰጣል
2. የዕፅዋት ዝርያዎች ዘር ያባዛል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል
3. የችግኝ ጣቢያ ያቋቁማል፣የብዜት ችግር ያለባቸው በዕፅዋት የማንበርና መልሶ የመተካት ዘዴ ላይ ምርምር ያደርጋል
4. የንብና የዕፅዋት ወንዴ ዘር ብናኝ የሚያሸጋግሩ የዕንስሳት ዝርያዎች መስተጋብር ላይ ምርምር ያካሂዳል
5. የሥነ ምህዳር ጥናት ቤተሙከራ ያደራጃል የከባቢ አየር ለውጥ በብዝኀ ሕይወት ሥነ ምህዳር ላይ ያለው ተፅዕኖ ላይ ምርምር ያካሂዳል
6. የአጭር ጊዜ ስልጠና ይሰጣል

**የፌስቡክ ገፃችንን**
Ethiopian Biodiversity Institute -EBI Like
**and follow ያድርጉ**
**ድረ ገፃችንን www.EBI.gov.et ይጎብኙ**

# የኢትዮጵያ ብዝኀ ሕይወት ኢንስቲትዩት



# ETHIOPIAN BIODIVERSITY INSTITUTE

**በህዝብ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ**

**2010 ዓ.ም**

# የሀገሪቱን የብዝኀ ሕይወት ሀብት በመጠበቅ የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እድገትና ዘላቂ ልማት እናረጋግጥ!

## የኢትዮጵያ ብዝኀ ሕይወት ማዕከላትና ጂን ባንኮች

ኢትዮጵያ ባላት የተለያየ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥና የአየር ንብረት ምክንያት ሰፊና የዳበረ የብዝኀ ሕይወት ሀብት ክምችትና ስብጥር የሚገኝባትና በዓለም ላይ ይህን መሰል ጸጋ ካላቸው ጥቂት አገሮች አንዷ ናት።
ይህ በዕጽዋት፣ በእንስሳትና በደቂቅ አካላት የሚካተተው የብዝኀ ሕይወት ሀብቷ ለሀገሪቱ ግብርና፣ ኢንዱስትሪና የጤና ዘርፍ ዕድገት እንዲሁም ለሌሎች ማሕበራዊና ልማት ነክ ተግባራት ከፍተኛ ድርሻ አለው።

ይሁን እንጂ የአየር ንብረት ለውጥ መከሰት፣ የድርቅና ምድረ በዳነት መስፋፋት፣ የህዝብ ቁጥር ከልማት ዕድገት ጋር ባልተመጣጠነ ሁኔታ መጨመር ይህን ሀብት መልሶ ለመተካት በማይቻልበት ሁኔታ ተጽዕኖ እያሳደረ መሆኑ ይታወቃል።

ዘርፈ ብዙ የሆነውን የሀገራችን የብዝኀ ሕይወት ሀብት ለማጎልበር፣ በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል እንዲሁም ከብዝሐ ሕይወት ሀብቱ ጋር ከተያያዘው የማሕበረሰብ ዕውቀት ጥቅም ተጋሪ ለመሆንና የሀብቱ ዋንኛ ባለቤት የሆነውን ሕብረተሰብ ለማሳተፍ የሚያስችል አቅም በመገንባት የበለጠ መስራት አስፈላጊ ነው።

በተጨማሪም የዓለም አቀፍ የብዝኀ ሕይወት ስምምነት ዓላማዎች መሰረት በማድረግ የሚወሰኑ ውሳኔዎችን ለመተግበር እና በሀገራችን ብዝኀ ሕይወት ሀብት ላይ እየደረሰ ያለውን አደጋ ለመቀነስ በክልሎችና በተዋረድ ባሉ የመስተዳደር እርከኖች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተቀባይነት አግኝቷል።

## ለማዕከላት መቋቋም መነሻ የሆኑ የአደረጃጀት ክፍተቶች

የብዝኀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት በአዋጅ ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር አንፃር የሀገሪቱን ብዝኀ ሕይወት መጠንና ስርጭት ማወቅ፣ ማጥናት፣ መጠበቅ፣ ማሻሻል፣ ማበልፀግና ለዘላቂ ጥቅም ማዋል ይጠበቅበታል። ይሁን እንጂ አደረጃጀቱ በፌደራል ብቻ በመወሰኑ
የሚከተሉት ዋና ዋና ችግሮች ይስተዋሉበት ነበር፤

- የብዝኀ ሕይወትን መመናመንና መጥፋት መንስዔዎችን በቅርብ ተከታትሎ ለመግታት አለመቻል፤
- እምቅ የብዝኀ ሕይወት ሀብቶቻችንን በትክክል ለይቶ ሀገራችን በምትፈልጋቸው የእድገት ዘርፎች በአግባቡ ጥቅም ላይ አለመዋል፤
- የብዝኀ ሕይወት ሀብት ባለቤት የሆነውን የአካባቢውን ማኅበረሰብ በቅርበት በማስተባበር የጀነቲክ ሀብት/ብዝኀ ሕይወት ስርቆትንና ህገወጥ ዝውውርን ለመግታት አለመቻል፤
- በብዝኀ ሕይወት ጥበቃና አጠቃቀም ላይ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶችን እስከ ኅብረተሰቡ/ ማኅበረሰቡ በማውረድ ተግባራዊ አለመደረግ፤
- የብዝኀ ሕይወት አገልግሎት ዋጋማነት በትክክል አለመታወቅ፤

ስለሆነም በኢንስቲትዩቱ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 120/1990፣ አንቀጽ 4 ላይ ‹‹የኢንስቲትዩቱ ዋና መ/ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል›› በሚለው ድንጋጌ መሠረትና በደንብ ቁጥር 291/2005 አንቀፅ 4 መሠረት የብዝኀ ሕይወት ጥበቃ ማዕከላትን በተመረጡ አካባቢዎች ተቋቁመዋል።

## የማዕከላቱ ዓላማ

ብዝኀ ሕይወት ለሀገራችን እድገት ቁልፍ አስተዋፅኦ ማድረግ ይችል ዘንድ በየክልሉ ውስጥ ያሉትን እምቅ የብዝኀ ሕይወት ሀብቶች በጥልቀት ማወቅ፣ መለየት፣ ዋጋማነታቸውን በመተመን ማንበርና በዘላቂታዊነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማመቻቸት፣

የብዝኀ ሕይወት ጥበቃ ማዕከላት በተዋረድ በመቋቋማቸው የብዝኀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት ተደራሽነት ለማስፋት።
ከዚህም በተያያዘ የሀብቱ ባለቤት የሆነው የአካባቢው ማሕበረሰብ/ሕብረተሰብ ብዝሀ ህይወትን ለመጠበቅ እና በዘላቂነት ጥቅም ላይ ለማዋል የሚኖረውን ተሳትፎ ለማሳደግ እድል ፈጥሯል።
ከዚህም ባሻገር የብዝኀ ሕይወት ጥበቃና አጠቃቀም ጥረት የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ባለድርሻ አካላትን በቅርብ በማስተባበር የተቀናጀና የተናበበ አሠራር ለመፍጠር ነው፡

ለዚህም በተዋረድ በተለያዩ አካባቢዎች የተቋቋሙት የብዝኀ ሕይወት ጥበቃና አጠቃቀም ማዕከላት የብዝኀ ሕይወት ሀብቶች ሀገራችን በምትፈልጋቸው የእድገት ዘርፎች ሁሉ ማለትም ለግብርና፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለጤና፣ ለሥርዓተ ምህዳርና አካባቢ ጥበቃ እንዲሁም ለሌሎች ማሕበራዊና ባህላዊ አገልግሎቶች እንዲውሉ ከፍተኛ ፋይዳ አላቸው።

የብዝኀ ሕይወት ጥበቃና አጠቃቀም ማዕከላት በሂደት በሁሉም ክልሎች በየደረጃው የሚቋቋሙ ሲሆን፤ ባለው የአቅም ውስንነት የተነሳ በቅድሚያ ትኩረት በተሰጣቸው የተወሰኑ አካባቢዎች ተቋቁመው የተሰጣቸውን ኃላፊነት በመወጣት ላይ ይገኛሉ።

እነዚህ አካባቢዎች የተመረጡባቸው ምክንያቶች፤

1. እስካሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚታወቀው የብዝኀ ሕይወት ክምችት፣ ስብጥርና ስርጭት ወካይነት/መናኸሪያነት (Hotspot Areas)፤ በምስራቅ አፍሪካ ከሚገኙት የብዝኀ ሕይወት መናኸሪያ ቦታዎች መካከል በኢትዮጵያ የሚገኙት ከፍተኛ ቦታዎች (ሰሜን ተራሮች፣ ባሌ ተራሮች) እና ዝቅተኛ/ረባዳ ቦታዎች (ሶማሌ አካባቢዎች፣ ምዕራብ ኢትዮጵያ) ሰፊውን ድርሻ ይይዛሉ።
2. በብዝኀ ሕይወት ሀብቶች ላይ እየደረሰ ባለው የመመናመንና የመጥፋት አደጋ ክብደት እና
3. የብዝኀ ሕይወት ጥበቃና አጠቃቀም ጅምር ሥራዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

በዚህ መሰረት የቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቷቸው የብዝኀ ሕይወት ጥበቃና አጠቃቀም የተቋቋመባቸው ማዕከላት የሚከተሉት ናቸው።

1. መቀሌ (ትግራይ እና አፋር አካባቢዎች)
2. ባህርዳር (አማራ አካባቢዎች)
3. መቱ (ጅማ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ማጂ አካባቢዎች)
4. ሀዋሳ (ደቡብ ህዝቦች አካባቢዎች)
5. ጎባ (አርሲ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ሸዋ እና በረና አካባቢዎች )